# የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን በልዩ መብት ከታክስና ከቀረጥ ነፃ ወይም በታክስና ቀረጥ ማስገባት ስለሚቻልበት ሁኔታ

## ዓላማው

- በመንግስት ሥራ፣ በትምህርት፣ በግል ሥራ፣ በስደት ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ባገኙት ሃብትና እውቀት ለአገራቸው ልማትና ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያደረጉ ለማበረታታት፣ በእድሜ የገፉ የጡረታ ዕድሜያቸውን ከወገናቸው ጋር እንዲያሳልፉ ለማስቻልና በውጭ ቆይታቸው ያፈሩትን ሃብት ይዘው እንዲገቡ ለመርዳት እንዲሁም በኢንቨስተርነት፣ በተራድኦ ስምምነት እና ለመጀመሪያ በኢትዮጵያ ለመኖር የሚመጡ የውጭ ዜጎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን የግል መገልገያ ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ፣ ከቀረጥና ከታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ እንዲያስገቡ ማስቻል ነው፡፡

## የግልና መገልገያ ዕቃዎች አገባብ

- ይህ መብት የተፈቀደላቸው ኢትዮጵያውያንና የውጭ ዜጎች እንደየምድባቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ያስገባሉ፡፡

## የባለመብቶቹ አመዳደብና የሚያስገኛቸው የቀረጥ ነፃ መብቶች

### ሀ. ምድብ አንድ

- በውጭ አገር በዲፕሎማትነት አገልግለው ሥራቸውን አጠናቀው ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ሥራቸውን አቋርጠው ወይም በጡረታ ወደ ሀገር የሚመለሱ፣
- በመንግሥት ጥሪ ወደ ሀገር የሚመጡ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን፣

### ለ. ምድብ ሁለት

- በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም የልማት ድርጅት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግለው ሥራቸውን አጠናቀው ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት አቋርጠው ወደ አገር የሚመለሱ ወይም፣
- ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለምአቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች በግላቸው ተወዳድረው የተቀጠሩና የዲፕሎማቲክ ማዕረግ የሌላቸው፣ ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግለው የሚመለሱ፣
- በውጭ ያፈሩትን ሃብት በአገር ውስጥ ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚመጡና የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው በውጭ አገር ኗሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ኢንቨስተሮች፣
- አንድ የትምህርት ዘመንና ከዚያ በላይ የከፍተኛ ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመለሱ፣

- ለአምስት ዓመትና ከዚያ በላይ በውጭ ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፣
- በተራድኦ ስምምነት መሠረት የሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች፣
- ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ አገር ሄደው ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ለምርምር ስራ በመካከሉ የሚመለሱ ተማሪዎች በዚህ ምድብ ተመድበው ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ከሚያመጡት ዕቃ ላይ ታሳቢ ሆኖ የሚያዝ መኪናን ሳይጨምር ከምርምር ስራው ጋር በተያያዘ የሚያስፈልጓቸው ዕቃዎች እየተመዘገቡ እንዲገቡ ይፈቀዳል፣ ለምርምር ሥራው የሚያስፈልጉ ሆነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2) ውስጥ ያልታቀፉ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ግን በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ከቀረጥ ነጻ በጊዜያዊነት የሚገቡ ይሆናሉ፣
- በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር የቅጥር/የሥራ ውል በማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማያስፈልጋቸው የንግድ ሥራዎች ላይ በመሰማራት እና ጡረታ ከወጡ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚመጡ ትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጪ ዜጎች፣

## መብቶች

- የምድብ አንድና ሁለት ተመላሾችና ባለመብቶች ማንኛውንም የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች (ኤሌክትሮኒክ፣ የሣሎንና የመኝታ ቤት ዕቃዎችን ከእያንዳንዱ አንድ አንድ በቁጥር ወይም እንደዕቃው ባህሪ በሴት አንድ) ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፣
- ስላይድ ፕሮጀክተር፣ 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ከ29 ኢንች በላይ የሆነ ቴሌቪዥን በልዩነቱ ላይ ቀረጥና ታክስ ከፍለው ማስገባት ይችላሉ፡፡

## ሐ. ምድብ ሦስት

- ከአንድ እስከ አምስት ዓመት በውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፣
- ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት ሰርተው የሚመለሱ ዲፕሎማቲክ ማዕረግ የሌላቸው የዓለምአቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች፣

## መብቶች

- የዚህ ምድብ ባለሃብቶች ቀረጥና ታክስ ከፍለው የሚያስገቧቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፣
- የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የሳሎን እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች ከየአንዳንዱ አንድ አንድ በቁጥር ወይም እንደ ዕቃው ባህሪ በሴት አንድ ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፣
- ኮንትሮል ቢሮ፣ የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ፣ የአየር ማስወጫና ሽታ መከላከያ፣ የመናፈሻ ወንበር፣ አልጋ፣ ድንኳን፣ የሳር ማጨጃ መኪና፣ የመፀዳጃ ቤት ገንዳ፣ ጄኔሬተር ባለ 4 ኪሎ፣ የመኪና ጐማና የመኪና ቸርኬዎች፣ ሃንድ-ቱል ሴት አነስተኛ፣ ስላይድ ፕሮጀክተርና 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥና ታክስ ከፍለው ማስገባት ይችላሉ፡፡

## *መ. ምድብ አራት*

- ሦስት ወር እና በላይ ከአንድ ዓመት በታች ውጭ አገር ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፣ የቅ/መ/ቤት ሠራተኞች፣ የዓለምአቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ባልደረቦች፣ እንዲሁም ለሥራ፣ ለሴሚናር፣ ለትምህርት፣ ለጉብኝት እና ለሕክምና ቆይተው የሚመለሱ፣

## *መብቶች*

- ከዚህ በታች የተጠቀሱት ቀረጥና ታክስ በመክፈል የሚያስገቡት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፡፡
- ከዚህ በታች የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የሳሎን እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች ከየአንዳንዱ አንድ አንድ በቁጥር ወይም እንደዕቃው ባህሪ በሴት አንድ ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፣
- ቁምሳጥን፣ ዓረቢያን መጅሊስ፣ ሶፋ፣ የመጠጥ/የዕቃ ማመላለሻ ጋሪ፣ የጋዝ ምድጃ፣ የጋዝ ስሊንደር ትልቁ፣ የውሃ ማሞቂያ፣ የባኞ ገንዳ፣ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት/መሮጫ/፣ የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ ሴት፣ ፒያኖ ለቤት ውስጥ አገልግሎት፣ ጊታር፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ የዕቃ ማጠቢያ ማሽን፣ የሳር ማጨጃ መኪና፣ ጄኔሬተር ባለ 4 ኪሎዋት፣ ሃንድ-ቱል ሴት አነስተኛ፣ ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ፣ የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞው፣ የመኪና ጎማ ከነቸርኬው ኮንትሮል ብሬ፣ የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ፣ የአየር ማስወጫ እና ሽታ መከላከያ/ኤር ኮንዲሽነር/ የመናፈሻ ወንበር፣ አልጋ፣ ድንኳን፣ የመፀዳጃ ገንዳ፣ ስላይድ ፕሮጀክተር እና 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥ እና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

## *ሠ. ምድብ አምስት*

- በትምህርት፣ በመንግሥት ሥራ፣ በሕክምና፣ በጉብኝት ወይም በሌላ ምክንያት ከሦስት ወር በታች ቆይተው የሚመለሱ ተመላሾች፣
- በውጭ ሀገር ከቤተሰብ ጋር በጥገኝነት ኖረው የሚመለሱ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን
- ስደተኞች፣

## *መብቶች*

- የዚህ ምድብ ተመላሾች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቀረጥና ታክስ ከፍለው ከሚያስገቧቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፣
- ቁምሳጥን፣ ዓረቢያን መጅሊስ፣ ሶፋ፣ የመጠጥ/የዕቃ ማመላለሻ ጋሪ፣ የጋዝ ምድጃ፣ የጋዝ ስሊንደር ትልቁ፣ የውሃ ማሞቂያ፣ የባኞ ገንዳ፣ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ብስክሌት/መሮጫ/፣

የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻ ሴት፣ የቤት ውስጥ ፒያኖ፣ ጊታር፣ አልጋ፣ ድሬሲንግ ቴብል የሳሎን ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ እስፕሪንግ፣ ቲቪ፣ ዴክ፣ ቪ.ሲ.ዲ.፣ ደስክ ቶፕ ኮምፒውተር፣ ላፕ ቶፕ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፣ ፍሪጅ፣ ቫክዩም ክሊነር፣ የፀጉር ካስክ፣ የፀጉር እስቲም፣ ቲቪ ራክ፣ የአዋቂ ብስክሌት፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ የዕቃ ማጠቢያ ማሽን፣ የሳር ማጨጃ መኪና፣ ጄኔሬተር ባለ 4 ኪሎዋት፣ ሃንድ-ቱል ሴት አነስተኛ፣ ሳተላይት ዲሽ ከነሪሲቨሩ፣ የልብስ ስፌት መኪና ከነዲናሞው፣ የመኪና ጎማ ከነቸርኬው፣ ኮንትሮል ብፌ፣ የመጽሐፍ መደርደሪያ ሼልፍ፣ የአየር ማስወጫ እና ሽታ መከላከያ/ኤር ኮንዲሽነር/፣ የመናፈሻ ወንበር፣ አልጋ፣ ድንኳን፣ የመፀዳጃ ገንዳ፣ ስላይድ ፕሮጀክተር እና 5 ሰው የሚይዝ ጀልባ ቀረጥ እና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

## *ማስታወሻ*

- ለየምድቦቹ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት ከተፈቀዱት የኤሌክትሮኒክስ፣ የሳሎን ቤትና የመኝታ ቤት ዕቃዎች በላይ በትርፍነት የሚመጡ የንግድ መጠንና ባህሪ የሌላቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው እንዲገቡ ይደረጋል፡፡
- በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1-6 ድረስ የተደነገጉት ቢኖሩም ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ ሞተር ሳይክል፣ ትልቁ የቡና ማሽን፣ ላሚኔተር፣ ባይንደርና ሌሎች ተመሳሳይ የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያዎች መጠናቸው ከአንድ ያልበለጠ ተገቢ ቀረጥ እና ታክስ ተከፍሎባቸው ሊገቡ ይችላሉ፡፡
- ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ፎቶ ኮፒ ማሽን (Personal grade desktop photocopy machine) ሲሆን አማካኝ አካላዊ መለኪያቸው፡
    - ወርዳቸው ከ16.05 ኢንች (40.44 ሴ.ሜ.) ያልበለጠ፣
    - ቁመታቸው ከ13.84 ኢንች (35.15 ሴ.ሜ.) ያልበለጠ፣
    - ክብደታቸው ከ36.47 ፓውንድ (17.64 ኪ.ግ.) ያልበለጠ፣
    - ስፋታቸው ከ18.77 ኢንች (47.68 ሴ.ሜ.) ያልበለጠ ሲሆን የልጡነቱ መጠን ከተገለፀው መለኪያ 10% መብለጥ የለበትም፡፡
- ‹የግል መገልገያ› ማለት ከአንድ ግለሰብ አገልግሎት ጥቅም እና ይዞታ ጋር የተቆራኘ በሕይወት ባለ ጊዜ ለአጭር ወይም ለረዥም ጊዜያት የሚጠቀምበት ተንቀሳቃሽ፣ ያገለገለ ወይም አዲስ ለንግድ የማይውል ዕቃ ነው፡፡
- ‹የቤት ውስጥ መገልገያ› ማለት በአንድ ጣሪያ ስር ከሚኖር ቤተሰብ ጥቅም፣ አገልግሎት፣ ይዞታ እና ፍጆታ ጋር የተቆራኙ በቤተሰቡ ጥቅም ላይ የቆዩ ወይም የሚቆዩ ያገለገሉ እና አዳዲስ ከቤተሰቡ ውጪ ለሌሎች ሰዎች አገልግሎት እና ጥቅም እንዲውሉ ያልታቀዱ ወይም ለንግድ የማይውሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን የሚያካትቱ ዕቃዎች ናቸው፡፡

- ለየምድቦቹ ከቀረጥ እና ታክስ በነፃ ለማስገባት ከተፈቀዱት የኤሌክትሪክ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የሳሎን ቤት እና የመኝታ ቤት ዕቃዎች በላይ በትርፍነት የሚመጡ የንግድ መጠን እና ባህሪ የሌላቸው የግል እና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ባለው ተቀፅላ 1 መሠረት ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

## *አገልግሎቱን ለማግኘት የመረጃ አቀራረብ*

- ተመላሾች በውጭ አገር የቆዩበትን ጊዜ ጠቅሰው ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን የሚገልጽ የመሸኛ ደብዳቤ ከነበሩበት አገር (እንደየአገሩ እና እንደየኑሮው ሁኔታ)፡-
  - ይኖሩበት ከነበረበት አገር የመኖሪያ ቦታ መቀየር፣ ይሰሩ ከነበረበት የሥራ ቦታ መልቀቁን፣
  - ጡረታ የወጣ ከሆነ ጡረታ መውጣቱን፣
  - ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የሚያስገቧቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ስደተኞች የጥገኝነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ በስደት ኖረው የሚመለሱ ወይም የጥገኝነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ወደ ሀገራቸው በሊሴፓሴ የሚመለሱ ከሆነ ማስረጃዎቻቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ኢንቨስተሮች ከኢትዮጵያ የተሰጣቸውን የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለኤምባሲው ወይም ለገቢዎች ሚኒስቴር የቀረጥ ነፃ መምሪያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ለትምህርት ሄደው የሚመለሱ የትምህርቱን አይነት፣ የቆይታ ጊዜ የትምህርቱን አቻ ግምትና አጠናቀው የሚመለሱበትን ጊዜ የሚገልጽ ከተማሩበት ተቋም የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

***ይህ መረጃ ለግንዛቤ ያህል በአጭሩ የተዘጋጀ በመሆኑ ስለዝርዝር ሁኔታው ከኤምባሲያችን ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡***